የመግለጫ ረቂቅ

ማስታወሻ

ይህ ረቂቅ የመደምደሚያ ጥሪዎችና ሃሳቦች አልያዘም። በዚህ መልክ ሰዎቹን ተቃውመን ለመውጣት ስምምነት ካለ በተጨባጭ በዚሁ መግለጫ በተለይ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ በሚለው ነጥብ ዙሪያ በነ ዶ/ር ታየም ሆነ በሲቲዝንስ ቻርተር ሰዎች በቀረቡት ሃሳቦች በጣም ተጨባጭ የሆኑ ነጥቦችን አስቀምጠን ድጋፍ ኮሚቴዎችም፣ ሌሎች ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎችም፣ የሲቪክ ስብስቦችም ወዘተ የሚንቀሳቀሱበት አቅጣጫ መጠቆም የግድ ነው። አለበለዚያ "መተቸት ብቻ ነው የህብረቱ ስራ" የሚለውን ትችት ማገዝ ይሆናል። በረቂቁና በመደምደሚያ መልክ ሊቀርቡ ስለሚችሉ ተጨባጭ ፕሮፖዛልስ በነገ (በሮቡ) ቴሌ ኮንፈራንስ ሃሳብ ይዘን ብንመጣ መግለጫው ተስተካክሎና የተስማማንባቸው ነጥቦች ተጨምረውበት አርብ ሊሰራጭ ይችላል።

# አስፍቶ ማየት! አርቆ ማየት!

የግንቦት ህዝባዊ እንቅስቃሴ በደም ባህር ብርታት ከተቀለበሰና የሽብርተኞች አገዛዝ ከተተከለ ወዲህ የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሳለንበት ብቻ ሳይሆን ቅልበሳው ከቀጠለ አይቀሬ ለሚሆነው የህዝባችንንም ሆነ የሃገራችንን ህልውና ሊፈታተን ለሚችለው አስከፊ የቀውስ አዙሪት የሚመጥን አፀፋ ሲሰጡ አይታዩም። በሃገራችን ከዳር እስከዳር ተቀስቅሶ የኢህአዴግን አገዛዝ ብርክ ካስያዘ በኋላ አደገኛ የሆነ የመፍዘዝ አዝማሚያ የሚያሳየው የግንቦት ህዝባዊ ማእበል በዚህ ቀጥሎ ሽንፈት ከመጣ ለሃገራችን ሰላም፣ አንድነትና ዴሞክራሲ ለማሰብ እንኳን የሚዘገንኑ መዘዞች እንደሚኖሩት ለመገንዘብ በሃገራችንም ሆነ በየትም አለም የተሸነፉ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎችን እጣ ፈንታ መመልከቱ ብቻ ይበቃል።

ዛሬ የምንገኝበት ቀውስ ዘርፈ ብዙ ቢሆንም ከዚህ ሁሉ አሳሳቢው በዴሞክራቶችና ሃገር ወዳዶች ጎራ የተሰለፉ ወገኖች ተገናኝተውና መክረው የጋራ ትግል ስትራቴጂ እንዲነድፉ በተደጋጋሚ የተደረጉ ጥሪዎች እስካሁን በተግባር አለመተርጎማቸው እንደሆነ ግልፅ ነው። የዚህ የአደገኛ ዳተኝነት አንዱ ምክንያት ሽብርተኛውን መንግስት ለመታገል ፍላጎቱም ወኔውም ሳያንሳቸው ነገር ግን ስለተያዘው ቅልበሳ አሳሳቢነት በቂ ግንዛቤ ከሌላቸውና በዚህም የተነሳ የጋራ ሳይሆን አንድዮሽ የትግል ስትራቴጂ እየቀየሱ ለመታገል የመረጡ ወገኖች በመከተል ላይ ያሉት አካሄድ ሆኖ እናገኘዋለን። ስንት ደምና እንባ ከተገበረበት የትግል ታሪካችን ምንም ትምህርት ያልቀሰመ ወይም ለመቅሰም የማይፈልግ የነዚህ ወገኖቻችን የከርሞ ጥጃ አካሄድ ከእይታ ስፋቱም ሆነ ከአርቆ ማየቱ አንፃር እጅግ ውሱን በመሆኑ የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ኢትዮጵያችን ሳለችበት አስከፊ ቀውስ የሚመጥን አፀፋ እንዳይሰጡ እያደረገ መሆኑ ከእለት እለት እያፈጠጠና እያገጠጠ የሚታይ ሃቅ ሆኗል።

በአለንበት ወሳኝና አጣዳፊ ወቅት ይህ ችግር በይሉኝታም፣ በዝምታም በቸልታም መታለፍ የሌለበት ጉዳይ በመሆኑ ከነዚህ ወገኖችና ከተከታዮቻቸው ጋራ በጥሞና ተወያይቶ ትግሉ ፈር የሚይዝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መሞከር ጊዜ ማጥፋት አይደለም። እንዲያውም የህዝባችንን የነፃነት ቀን ለማፋጠን የሚረዳ ጤናማ አካሄድ ነው። በዝባዝንኬና እጅ እግር በላላቸው "ልዩነቶች" ሳይሆን በእይታና ፖለቲካዊ ይዘት ባላቸው ቁምነገሮች ላይ ፍርጥርጥ አድርጎ ለመከራከር መሞከር የተቃዋሚውን ጎራ መከፋፈልና ማዳከም አይደለም። እንዲያውም በግልፅ አጀንዳና በግልፅ አካሄድ ላይ የተመሰረተ ከብረት የጠነከረ የታጋዮች አንድነት ለመመስረት የሚረዳ ፍቱን አካሄድ ነው። በመሆኑም ዛሬ ህብረታችን ለመስጠት የተገደደው ይህ መግለጫ በዚህ መንፈስ የሚቀርብና የሃገራችን ዴሞክራቶች መክረውና ዘክረው ትግላችን ግልፅ በሆነ አጀንዳ ተጠናክሮ እንደገና የሚያንሰራራበትንና የሚቀጥልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ለሚያስፈልገው ውይይት አስተዋፅኦ ለማድረግ የቀረበ ሰነድ መሆኑን ከወዲሁ ለማስረገጥ እንወዳለን።

ህብረታችን ይህ ነው የማይባል ደምና እንባ የፈሰሰበትን የህዝባችንን የድምፄ ይከበር አጀንዳ አንግበን ለዚህ ሰ
ማእት ህዝባችን የጋራ አመራር ለመስጠት እንንሳ እያለ ሲወተውት በዚህ አጣዳፊ ጊዜ አመት ተኩል በላይ እንዳስቆጠ
ረ ሁሉም የሚያውቀው ነው። ለዚህ ቅንና ሃገራዊ ጥሪ የዝሆን ጆሮ ሲሰጡ ከቆዩ አንዳንድ ወገኖች መሃከል የቅንጅት
አለም አቀፍ አመራር ወገኖቻችን በአለፉት ሳምንታት የታሰሩት መሪዎቻችንን ሌሎች የህሊና እስረኞችን የማስፈታቱን
ጉዳይ "ለኛ ተውት" በማለት በጠባብ ድርጅታዊ አጀንዳ ብቻቸውን ተንቀሳቅሰው ለማንቀሳቀስ ሲሞክሩ ታዝበናል። ከ
ዚህ አልፎ ተርፎ ደግሞ አሁን እንደምናየው በሃገራችን ሚልዮኖችን ለግንቦት አላማቸውና አጀንዳቸው የማንቀሳቀሱ
ጥሪ በፖለቲካ፣ በስነልቡናዊም ሆነ በዲፕሎማሲያዊ ምክንያቶች ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት አልፎ የሁሉም ዴሞክራ
ሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከፖለቲካ ድርጅቶችም ዘልቆ የተለያዩ የሲቪክ፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የሃይማኖት ስብስ
ቦችና የሃገር ሽማግሌዎች ሰፊ ምክክር የተደረገበት የጋራ ጥሪ መሆን አለበት እያልን እኛም ሆንን ስፍር ቁጥር የሌላቸው
ሃገር ወዳድ ሃይሎች ሲወተውቱ እንዳልቆዩ ሁሉ የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ለብቻው አንድ የትግል ጥሪ ለኢትዮ
ድያ ህዝብ አስተላልፏል።

አርብ የካቲት 2 በተበተነና ለሃገራችን ወጣቶች በየትምህርት ተቋሞቻቸው የመምከርም ሆነ የመዘጋጀት ፋታ
እንኳን በማይሰጥ መግለጫ በመላ ኢትዮጵያ "ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት" ያሉ ተማሪዎች ከሰ
ኞ የካቲት 5 ቀን ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ትምህርት እንዲያቆሙ፣ በዚህ ሳምንት ውስጥ መንግስት ለህዝቡ ጥያቄ አወን
ታዊ ምላሽ ካልሰጠ አድማውን ለመቀጠል "ከቅንጅት የሚሰጡ ተከታታይ መመሪያዎችን እንዲጠባበቁ" ጥሪ ቀርቧል
። ከዚህ አልፎ ተርፎ ደግሞ በመላ ሃገሪቱ ከተሞች የሚኖሩ ዜጎች በአንዲት በተወሰነች ቀንና ከዚህ እስከዚህ ባለ የተ
ወሰነ አራትም አምስትም ሰአት ሳይባል በደፈናው "መሪዎቻችን እስኪፈቱ ድረስ በእረፍትና ከስራ ሰአት ውጭ የኢትዮ
ጵያን ከተሞች ጭር በማድረግ" እምቢተኝነታቸውን እንዲገልፁ ተጠይቋል። "ከስራ ሰአት ውጭ" በኛም ሆነ በማንም
ህብረተሰብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ተግባራትና ግዴታዎች እንዳሉ እየታወ
ቀ ሳልተወሰነ ጊዜ ይህንን ሁሉ ወደ ጎን ትታችሁ ከተሞችን ርጭ አርጉ የሚለው ገና ከጥንስሱ የሞተ ጥሪ ማስተላለፍ
አስገራሚ ብቻ አይደለም። ጨርሶ ሃላፊነት የሚጎድለውም አካሄድ እንደሆነ ማንም አእምሮ ያለው ሰው የሚረዳው ይ
መስለናል።

እንደዚህ አይነቱ አካሄድ ሃገራችን ዛሬ በግንቦት ቅልበሳ ማግስት ያለችበትን ሁኔታ አሳሳቢነት ብቻ ሳይሆን በ
ጋራ ትግል ይህንን ቅልበሳ ከህዝባችን ጋር ታግለን ካልቀለበስነው እንደ የካቲት ማግስት ሃገራችን ልትገባበት የምትችል
ውን አሰቃቂ የቀውስ አዙሪት ያላገናዘበ አሰራር ነው ብለን እናምናለን። በመሆኑም ለነዚህ ወገኖቻችንና በአጠቃላይ ለ
ኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ከዚህ ይልቅ "አስፍቶ ማየት! አርቆ ማየት!" በሚል መንፈስ ያለንን አስ
ተሳሰብና አቋም በአጭሩ ለማስቀመጥ እንወዳለን።

ዛሬ በግንቦት ቅልበሳ ማግስት ሃገራችን ያለችበት ሁኔታ ምን ይመስላል? እኛም መላው አለምም እንደሚያውቀ
ው ህዝባችን ታግየ የተጎናፀፍኩትን ድል ሰቀማ ታግየ አስመልሳለሁ ብሎ በመንቀሳቀሱ በመቶ የሚቆጠሩ ንፁህ ዜጎች
በጠራራ ፀሃይ ተረሽነዋል፣ ሌሎች "ቤት ይቁጠራቸው" የሚባሉ በግፍና በገፍ ተገድለው ጅምላ መቃብር ተጥለዋል፣ በ
ደርዘን ሽህ የሚቆጠሩ ሌሎች ለእስር ተዳርገዋል፣ የህዝባችንን ትግል ለማዝረክረክ ሆን ተብሎ በተጠነሰሰ ሴራ መሪዎ
ቹና ተመራጮቹ ከሞቀ ቤታቸው ታፍሰው ወህኒ ተወርውረዋል፣ ከግንቦት በፊት የነበረችውን የፕሬስ ነፃነት ፍንጭ ለ
ማውደም በደርዘን የሚቆጠሩ ጋዜጠኞች ታስረዋል፣ ከእስር የተረፉት ስራና የኑሮ ዋስትና ተነፍገው ከነቤተሰቦቻቸው ለ
ርሃብና ለማጣት ተዳርገዋል። የተያዘው አስከፊ የሆነ የቅልበሳ ሂደት ነውና የኢህአዴግ መሪዎች የአፈና ውርጅብኝ በነ
ዚህ "አይን በሚስቡ" የግፍ ድርጊቶች የሚወሰን ወይም የሚቆም አይደለም።

በህብረታችን ሁለተኛ ሸንጎ በትክክል እንደጠቆምነው በመተከል ላይ ያለው የሽብር አገዛዝ ነውና ዛሬ አይን
ከሚስበው የከተማ ሃይሎች አፈና በማያንስና እንዲያውም ከዚያ በሚከፋ ሁኔታ በመላ ሃገሪቱ በግንቦት ግንባር ቀደም
ሃይሎች ላይ ብቻ ሳይሆን "ያኔ በምርጫው ጊዜ ይህንን ወይም ያንን ተቃዋሚ ሃይል ደግፈሃል፣ ለዚህ ወይም ለዚያ ተ
ቃዋሚ ሃይል ድምፅ ሰጥተሃል" እየተባሉ ገበሬዎች፣ ሰራተኞች፣ ወጣቶች፣ ሴቶችና ሌሎች ዜጎች በጨካኝ የኢህአዴ
ግ ካድሬዎችና ሹማምንት ይህ ነው የማይባል ግፍ እየተፈፀመባቸው ነው። በአለፈው ወር የወጣው የሁማን ራይትስ ወ

ች የተባለው አለም አቀፉዊ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት "ትኩረቶች አዲስ አበባ ላይ ቢሆኑም" ከዋና ከተማዋ ውጭ ስለሚካሄደው አፈና ሲያትት በኦሮሚያ የኦነግና የኦብኮ ደጋፊዎች በመባል አሁንም ዜጎች እንዴት እንደሚታፈሱ፣ በአማራው ክልል የተቃዋሚ ደጋፊ ወይም "አላስተማማኝ" እየተባሉ ገበሬዎች እንዴት ማዳበሪያ እንደሚከለከሉ፣ እንዴት ከመሬታቸው እንደሚነቀሉ፣ እንዴት በውድቅት ሌሊት ቤታቸው እየተሰበረ እንደሚገረፉ ወይም ለእስር እንደሚዳረጉ በዝርዝር አስቀምጧል። ይህ በመላ ሃገሪቱ የሚንንፀባረቅ አስከፊ ክስተት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

ከዚህ ተነስተን ነው ዛሬ በሃገር ወዳዱና በዴሞክራቱ ጎራ ተሰልፈን ለዚች አገር ደህንነት በመዋደቅ ላይ ያለን ዜጎች ሳለንበት ሁኔታ የሚመጥን አፀፋ ለመስጠት እንድንችል መጀመሪያ አስፍተን እንይ የምንለው። አስፍተን እንይ ስንል ምን ማለታችን ነው?

አስፍተን እንይ ስንል መጀመሪያ የግንቦትን ድል ባለቤትና የቅልበሳውን ሰለባዎች ማንነት በሚገባ እንወቅ ማለት ነው። ቅንጂት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ በግንቦቱ ምርጫ በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ድምፃቸውንና አመኔታቸውን የሰጡት ድርጅት እንደነበረ አይካድም። ነገር ግን እኛ ነገሩን አስፍተን የምናይ ሃይሎች ይህንን ተገኝቶ የነበረውን ድል የአንድ ወይም የሁለት ድርጅቶች ድል ብቻ አድርገን አናየውም። ይህ ድል ከሁሉም ከሁሉም በላይ የህዝባችንና የዴሞክራሲ ድል ነበር ብለን እናምናለን። ይህንን ሃቅ ከተቀበልን የቅልበሳውን መዘዝ ገፈት ማን እየተጋተ ነው? ለሚለው ተጨባጭ ጥያቄ መልሳችን እገሌ ከገሌ ሳይባል ድል አድራጊ የነበረው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው የሚል መልስ ነው። የግንቦት ድል የሚልዮኖች ድል እንደመሆኑ መጠን ሽንፈትና ቅልበሳ ሲመጣ ደግሞ የዚህን መዘዝ ገፈት የሚቀምሱት እነዚሁ ሚልዮኖች ይሆናሉ ስንል የየካቲትም ሆነ የሌሎች በሌላው አለም የተሸነፉ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች እጣ ፈንታ ባሳየው አሳዛኝ የታሪክ ሃቅ ብቻ ተመርኩዘን አይደለም። ዛሬ በግንቦት ማግስት የምናየው ይህንኑ መራራ ሃቅ ነው። ቅልበሳው በሃገር የመጣ በመሆኑ አስፍቶ ማየት ስንል ይህ የቅልበሳውን መዘዝ ገፈት በመቅመስ ላይ ያለው ዜጋ በሙሉ በአንድነት እንደ አንድ ሰው የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል ማለት ነው።

ሁለተኛ አስፍቶ ማየት ማለት ዛሬ በሃገራችን በመውረድ ላይ ያለው የአፈና ውርጅብኝ መሰረታዊ ምንጩ ይህ የተያዘው የቅልበሳው ሂደት ስለሆነ አፈናው እንዲቆም፣ መሪዎቻችን እንዲፈቱ እያልን የምናካሂደውን ተገቢ ተጋድሎ ለአንዲት ሰከንድ እንኳን ቢሆን የግንቦትን ድሎች ለማስመለስና የተኮላሸውን የዴሞክራታይዜሽን ሂደት መልሶ በእግሩ ለማቆም ከሚደረገው ህዝባዊ ተጋድሎ ነጥለን ማየት አንችልም ማለት ነው። ትግላችን በዚህ ሰፊ በሆነ ህዝባዊ አላማ ተንቀሳቅሶ የኢህአዴግን መንግስት እንዲያፈገፍግ የሚያስገድድበት ደረጃ ካልደረሰ ለእስር የተዳረጉትን ወገኖቻችንን ማስፈታትም ሆነ የተነጠቁ መብቶቹን ማስመለስ ቀርቶ በህዝባችን ላይ የሚዘንበውን የቀጣይ አፈናውን ውርጅብኝ የምናቆምበት ምንም ተአምር አይኖርም ማለት ነው።

ሶስተኛ አስፍቶ ማየት ማለት የግንቦትን ድሎች ለማስመለስ በሚለው ጉዳይ የጋራ ግንዛቤ ከተደረሰ ይህ ድል የሚልዮኖች እንደመሆኑ መጠን ተመልሶ የሚገኘው በሚልዮኖች ትግል ብቻ እንጂ በጥቂት "ግንባር ቀደም" ነን ባዮች ግርግር ወይም በአለም አቀፍ ኮሙኒቲ ተብየው ነገር ግፊት ጨርሶ እንደማይሆን መገንዘብ ያስፈልጋል ማለት ነው። ይህንን ከተቀበልን ደግሞ የማናመልጠው መደምደሚያ ይኖራል። ሚልዮኖችን እንደ አንድ ሰው ተንቀሳቅሳችሁ ጭቆናን ተቋቋሙ፣ ድላችሁን አስመልሱ እያልን ጥሪ እያደረግን አሁን የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ወገኖቻችን እንደሚያደርጉት "እንደ አንድ ሰው ግን በኛ ስር ተነስ" ከሚለው አደገኛና ዞሮ ዞሮ ደግሞ ተወደደም ተጠላም ታውቆም ሆነ በፖለቲካ ጨቅላነት የትግሉን አንድነት በማስተጓጎል በቀጥታ ለኢህአዴግ ፀረ ህዝቦች ከሚሰራ አደገኛ አካሄድ መጠንቀቅ፣ ከዚህ ይልቅ ግንባር ቀደም ነኝ ብሎ "እጅ ለእጅ ተያይዘን እንታገል" እያለ ጥሪ የሚያስተጋባው ወገን ሁሉ መጀመሪያ ራሱ በአንድነት ቆሞ  አርአያነቱን ማሳየት ያስፈልገዋል ማለት ነው።

ይህ ካልሆነ ሌላ ምንም መጠሪያ አናገኝለትም። በእሳት መጫወት ነው። የየካቲት ቅልበሳ በሃገራችን ሰላም፣ ዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን በአንድነቷ ጉዳይ ያደረሰውን መዘዝ ስለምናውቀው ገጣቢትን ያዩ ወይም አይተው እንዳላዩ በእሳት የሚጫወቱ ወገኖች ስናይ እኛ ከአለፈው ታሪካችን ትምህርት ቀስመናል የምንል ዜጎች ደግሞ "በቃ" ማለት ሃገራዊ ግዴታችን ነው ብለን እናምናለን። ከዚህ ከቀሰምነውና ማንም ዛሬ በትግል ላይ "አለሁ" የሚል ሃይል ሁሉ መቅሰም አለበት ከምንለው መራራ ትምህርት ስንነሳ ማስተላለፍ የምንፈልገው አንድ መልእክት ብቻ ነው። የቅልበሳውን ሂደ

ት ሊያቆመው በሚችል አንድና አንድ ብቻ በሆነው የጋራ ትግል መንገድ ካልጎዝን እኛም ሃገራችንም፣ ህዝባችንም ወ ደ ጥፋት እየሄድን ነው።

በዚሁ ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ሁሉም ራሱን መጠየቅ ያለበት አንድ መሰረታዊ ጥያቄ አለ። ይኸውም ህዝባችን በ ጋራ ተንቀሳቅሶ በጊዜ ካላቆመው የኢህአዴግ መሪዎች ምን ገዷቸውና ማን አስገድዷቸው ነው የተያያዙትን የቅልበሳና የጥፋት ፋይል የሚዘጉት? የሚለው ጥያቄ ነው። በአጓጉልና አደገኛ የህልም አለም ውስጥ ስለማንኖር ለዚህ የምንሰጠ ው መልስ አጭርና ዘግናኝ ነው። ማንም አያቆማቸውም። ይቀጥሉበታል። ይህንን ካልን ደግሞ ህዝባዊው ትግል በኢህ አዴግ ሽብር ብቻ ሳይሆን በአመራር ክፍተትና ዝርክርክነት ከተኮላሸ ሃገራችን የዛሬ አመት፣ የዛሬ ሁለት አመትም ሆነ የዛሬ አምስትም አስርም አመት የት ነች? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። አርቆ ማየት የምንለው የትግል ስትራ ቴጂያችንን ስንቀይስ ዛሬ በአይናችን ስር ከምናየው አስከፊ ክስተት ብቻ ሳይሆን "ሁኔታው ከቀጠለ ወዴት ያመራል?" ከሚለውም ስሌት መነሳትም እንዳለብን ለመጠቆምም ነው።

ምርጫ በራሱ የፖለቲካ ፕሮግራም አይደለም። ቅንጅትም ሆነ ህብረታችን በግንቦት ምርጫ ሲሳተፉ ሃገራችን ፊት ለተደቀኑ ከባድ ከባድና የሰማይ ስባሪ ለሚያክሉ "ኢትዮጵያችንን እንደ ሃገር፣ ህዝባችንን እንደ ሰብአዊ ፍጡር" ህልውናቸውን ለሚፈታተኑና ዙሪያ ገጠም ለሆኑ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የአካባቢ ቀውሶች የፖሊሲ አማራጮች አን ግበው እንደነበረ ይታወቃል። መናጢ ድህነትም ሆነ የጅምላ ስራ አጥነት፣ ዘመን አመጣሹ ኤች አይቪ ኤይድስም ሆነ ሌሎች ሳይንስ ሊረሳቸው የቃጣቸው የብሉይ ዘመን በሽታዎች፣ የአካባቢ ውድመትም ሆነ ትውልድ ገዳይ ብለን የፈረ ጅነው የትምህርት ፖሊሲ ወዘተ እየተጋገዙና አንዱ "የሌላው መነሾም ውጤትም እየሆኑ" ወደ ጥፋት እየሄድን ነው ብለን በዴሞክራሲያዊና አገራዊ ፖሊሲዎቻችን ዙሪያ ህዝባችንን ቀስቅሰናል። የኢህአዴግ መንግስት "አሸነፍኩ" ሲል በአንድ መልኩ እነዚህን (ዛሬ ባለው ወከባ ምክንያት በተቃዋሚው ጎራ ማንም የማያነሳቸውን) አጥፊ ፖሊሲዎች እገፋ ባቸዋለሁ ማለቱ እንደሆነ ግልፅ ነው። ነገ የኢህአዴግ መሪዎች በአንድ በኩል ህብረተሰባችንን በሽብር ስላንበረከኩና በሌላ በኩል ደግሞ በባእድ አሳዳሪዎች ፊት ሳለመጋለጥ ሲሉ ብቻ የአፈናው ውርጅብኝ አይን በሚስብ መልኩ ሊረግ ብ ይችላል። ነገር ግን እነዚህ አገር ገዳይ ፖሊሲዎች ስለሚቀጥሉ የኢትዮጵያችን የመከራ ዘመን ተባብሶ እንደሚቀጥ ል ለመተንበይ ጠንቋይ መቀለብ የሚያስፈልግ አይመስለንም።

ከዚህ አስከፊ መፃኢ እድል አንፃር አንፃር አርቆ ማየት ማለት ሃገራችን ልክ እንደየካቲት ማግስት ለማሰላሰል እንኳን የሚቀፉ የቀውሶች አዙሪት እየገባች እንደሆነ መገንዘብና ለዚህ ሁኔታ ለሚመጥን ተጋድሎ ራስን ማዘጋጀት ማ ለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ አንደኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ከምስኪን፣ ጠባብና እየገባንበት ካለነው ቀው ስ አንፃር ሲታይ "እዚህ ግባ" ሊባል ከማይችል የአንጃም ሆነ ድርጅታዊ አጀንዳ ተቆጥበው ቅልበሳውን በጋራ ተጋድሎ ለመቀልበስ ይነሳሱ፣ ሁለተኛ ለሃገራችንንና ለህዝባችን ሊከተሉ ከሚችሉት ዘግናኝ ቀውሶች አንፃር ትግላቸውን "ይቻ ሳል" በሚል ዘይቤ ብቻ ሳይሆን "ምርጫ የለም! መቻል አለበት!" በሚል ፅናትና ቁርጠኝነት ይያያዙት፣ ሶስተኛ ይህንን ትግል "ብሩህ ተስፋን" እውን ለማድረግ በሚል የነገ ቅንጦት በሚሻ መንፈስ ብቻ ሳይሆን እናት አገራችንንና ይህንን ሰማእት ህዝባችንን ከአይቀሬና አስከፊ ጥፋት ለማትረፍ በሚል አልሞት ባይ ተጋዳይነት ብቻ ሊሰጠው በሚችለው ጉ ልበት፣ ድፍረትና ፅናት ይዋደቁ ማለታችን ነው።

አርቆ ማየት ማለት ቅልበሳውን በዚህ መልክ ታግለን በጊዜ ካልቀለበስነው ሃገራችን አስከፊ የሆነ የቀውስ አዙ ሪት ውስጥ ትገባለች ማለት ብቻ አይደለም። ከጊዜ ጋር ትግላችን ከእለት እለት የአቀበት ጉዞ የሚሆንበትም አደጋ እን ዳለ መገንዘብ ይኖርብናል። ቀውሱ፣ ወከባው፣ ቅልበሳው እየከፋ በሄደ ቁጥር የጋራ አማራጭና አመራር በሌለበት ሁኔ ታ ይህ ብቻውን ህዝባችንን ለትግል ያነሳሳዋል ማለት አደገኛ ህልም ነው። እርግጥ ስለወከባውና ስለ ቀውሱ ክፋት የዚ ህ ሁሉ ገፈት ቀማሽ ለሆነው ህዝባችን ለቀባሪ ለማርዳት በሚግደረደሩ ፋይዳ ቢስ መግለጫዎች የኢህአዴግን መሪዎች ግፍ "እያጋለጥን" መቀጠል እንችላለን። ይህ ግን ውጤት ይኖረዋል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በወቅቱ ያልተቀለበሱ ቅልበሳዎች ከባድ ከባድ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የፖለቲካ ቀውሶች በማዝነብ ብቻ አይወሰኑም። ቀውሱ በከፋ ቁጥር በወከባና በሽብር አንገቱን በደፋና በአመራር መዝረክረክ ግራ በተጋባ ህብረተሰብ ውስጥ የሚሰፍነው ጨለምተኝነት የ ዚያን ህብረተሰብ የአፀፋ የመስጠት ወይም ሪአክት የማድረግ አቅም እንደሚያሟሽሸውም ትላንትና የየካቲት ማግስት ያ

ሳየንና ዛሬም በግንቦት ማግስት ዳርዳር ማለት የጀመረን የትግል ትጥቅ መፍታት አደጋ ከፊታችን እንደተደቀነ ጠንቅቆ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ይህንን መገንዘብ ማለት በግንቦት የታየውን የህዝብ ንቃትና የትግል ወኔ "እንደ ዘልአለማዊ ግኝት" ለመውሰድ ከሚግደረደር አስተሳሰብ መቆጠብና ይህም በጎ ግኝት እንደ ድምፁ፣ እንደ መብቱ ከህዝባችን በአመፅ ሊነጠቅ እንደ ሚችል መረዳት ያስፈልጋል። ኢህአዴግ በአመፅ ሊደመስሰው የተነሳውን ከጦር የሚፈራውን ይህንን የህዝብ የትግል ወ ኔ እኛ ደግሞ ባለማወቅ እየተፈታተንን እንዳናከስመው ከፈለግን ብዙ አማራጭ የለንም። በግንባር ቀደም ነኝ ባዩ ሰፈር ህዝብን ግራ ከሚያጋባና "ሁሉም አይረቡም" ወደሚል ድምዳሜ ከሚገፋፉ ማንኛውም ድርጊት ተቆጥበን፣ ትግሉ ከጊ ዜም ጋር እንደሆነ ጠንቅቀን በመረዳት ዳተኝነትን አሽቀንጥረን ጥለን በህዝባችን ፊት እጅ ለእጅ ተያይዘን አርአያነት ያለው የጋራ ትግል ማካሄድ ይጠበቅብናል።